## ከዲኑ ፡ የተሰጠ ፡ ዓመታዊ ፡ መግለጫ ፡

## ፲፱፻፷ ፡ ዓመተ ፡ ምህረት ።

ኲዊንቲን ፡ ጆንስተን — በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ መምህር ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ (ፋኩልቲ) ፡ ዲን ።

ይህ ፡ መግለጫ ፡ የተዘጋጀው ፡ የ፲፱፻፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የትምህርት ፡ ዓመት ፡ ሲፈጸም ፡ ሲሆን ፡ የተዘጋጀውም ፡ ለቀድሞ ፡ ተማሪዎቻችንና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙት ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ወዳጆች ፡ ነው ። የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ እያደገ ፡ የሥራ ፡ ፍሬያችን ፡ እየሠመረ ፡ እንዲሄድ ፡ የነዚሁ ፡ ወዳጆቻችን ፡ ምክርና ፡ እርዳታ ፡ ያስፈልገናል ። እርዳታና ፡ ምክራቸውም ፡ እንዳይለየን ፡ የምናከናውናቸውን ፡ ተግባሮችና ፡ የሚያጋጥሙንን ፡ ችግሮች ፡ እንዲያውቁልን ፡ ያስፈልጋል ። የሚከተለው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ የፈጸማቸውን ፡ ተግባሮችና ፡ ወደፊት ፡ የሚያጋጥሙትን ፡ ችግሮች ፡ የሚያሳይ ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ ነው ።

<u>የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ።</u> ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ከተፈጸሙት ፡ ተግባሮች ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ ማህበር ፡ መቋቋም ፡ ነው ። ለጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ረቂቅ ፡ የሚከተሉት ፡ አባሎች ፡ አቶ ፡ አቢዩ ፡ ገለታ ፡ ከበደ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ መስፍን ፡ ፋንታ ፡ ሰላሙ ፡ በቀለ ፡ ሽመልስ ፡ መታፈሪያ ፡ ባሉበት ፡ ኮሚቴ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በክረምቱ ፡ ወራት ፡ መግቢያ ፡ ላይም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የምሳ ፡ ግብዣ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ቍጥራቸው ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ የሚሆን ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ አራት ፡ ሰዓት ፡ የቆየ ፡ ስብሰባ ፡ አድርገው ፡ የመመሥረቻውን ፡ ጽሑፍ ፡ ረቂቅ ፡ አንቀጽ ፡ በአንቀጽ ፡ ከተከራከሩበት ፡ በኋላ ፡ አንዳንድ ፡ ማሻሻያዎችን ፡ በመተካት ፡ አፀደቁት ። በማኅበሩ ፡ ደንብም ፡ መሠረት ፡ መኖሪያው ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ውጭ ፡ ቢሆንም ፡ ከሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከዲግሪ ፡ ሆነ ፡ ከዲፕሎማ ፡ ወይም ፡ ከሰርቲፊኬት ፡ ክፍል ፡ ተመርቆ ፡ የወጣ ፡ ማናቸውም ፡ ተማሪ ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ ሙሉ ፡ መብት ፡ አለው ። መሥራች ፡ አባሎች ፡ በተገኙበት ፡ ስብሰባ ፡ የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ከፀደቀም ፡ በኋላ ፡ አቶ ፡ አቢዩ ፡ ገለታ ፡ የማኅበሩ ፡ ፕሬዝዳንት ፡ ሆነው ፡ ተመርጠዋል ።

ትምህርት ቤታችን በጉጉት ፡ አትኩሮ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ከፍተኛ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ለመከታተል ፡ ወደውጭ ፡ አገር ፡ የሄዱትን ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ ነው ። በዚህ ፡ በያዝነው ፡ ዓመት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የነበሩት ፡ የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡ — መብራቱ ፡ ዮሐንስ ፡ ማጊል ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ሞንትሪአል ፡ ካናዳ ፤ ኢያሱ ፡ አያልቅበት ፡ ኃይሉ ፡ መኰንን ፡ እና ፡ ያዕቆብ ፡ ኃይለማርያም ፡ ካሊፎርኒያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ሎስ ፡ አንጀሊስ ፤ አሌክሳንድራ ፡ ሐማዊ ፡ ለንደን ፡ ዩኒቨርሲቲ ። በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ለመከታተል ፡ ዕድል ፡ ያገኙት ፡ ደግሞ ፡ አባቢያ ፡ አባጆቢር ፡ በማጊል ፡ ዩኒቨርሲቲ ፤ ሽመልስ ፡ መታፈሪያ ፡ በቺካጐ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ቺካጐ ፡ ኤሊኖይስ ፤ ዮሐንስ ፡ ኅሩይ ፡ ኢንስቲቲዩት ፡ አብ ፡ አድቫንስድ ፡ ሊጋል ፡ ስተዲስ ፡ ለንደን ፤ ዘርዓይ ፡ ኃብተ ፡ ሥላሴ ፡ በአሐዮ ፡ ስቴት ፡ ዩኒ

ቨርሲቲ ፡ ኦሐዮ ፣ ዘገየ ፡ አስፋው ፡ በዊስኮንሲን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ማዲሰን ፡ ዊስኮንሲን ፣ ናቸው ።

<u>ተማሪዎች</u> ። የ፲፱፻፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የትምህርት ፡ ዓመት ፡ ሲጀመር ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚሰጠውን ፡ ትምህርት ፡ ለመከታተል ፡ ፫፻፪ ፡ የዲግሪ ፡ ተማሪዎች ፡ ፪፻፺፯ ፡ የዲፕሎማ ፡ ተማሪዎች ፡ እና ፡ ፪፻፲፬ ፡ የሰርቲፊኬት ፡ ተማሪዎች ፡ ተመዘገቡ። ከዚሁም ፡ ውስጥ ፡ ፺፪ቱ ፡ አዲስ ፡ የተከፈተው ፡ የገሚስ ፡ ጊዜ ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ ተማሪዎች ፡ ሲሆኑ ፡ ፩፻፷፫ቱ ፡ ደግሞ ፡ በሐረር ፡ የተከፈተው ፡ አዲስ ፡ የሰርቲፊኬት ፡ ክፍል ፡ ተማሪዎች ፡ ናቸው ። መደበኛው ፡ የትምህርት ፡ ዓመት ፡ ከተጀመረ ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ በጂማ ፡ በአሥመራና ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተሞች ፡ ፲፻፳፮ ፡ ተማሪዎች ፡ የሚገኙበት ፡ ተጨማሪ ፡ የሰርቲፊኬት ፡ ክፍል ፡ ተከፈተ ።

ያለፈው ፡ የትምህርት ፡ ዓመት ፡ ሲፈጸም ፡ ፲፯ ፡ ተማሪዎች ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ በማግኘት ፡ ሲመረቁ ፡ ፺፱ ፡ ደግሞ ፡ የሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ በማግኘት ፡ ተመርቀዋል ። ትምህርታቸውን ፡ ያጠናቀቁ ፡ የሰርቲፊኬት ፡ ተማሪዎች ፡ ባለመኖራቸው ፡ በዘንድሮው ፡ ዓመት ፡ ከሰርቲፊኬት ፡ ክፍል ፡ የተመረቁ ፡ ተማሪዎች ፡ አልነበሩም ።

የሚከተሉት ፡ ተማሪዎች ፡ በትምህርታቸው ፡ ከፍተኛ ፡ ውጤት ፡ ስላመጡ ፡ ሽልማት ፡ አግኝተዋል ፡ ፋሲል ፡ ናሆም ፡ የቻንስለር ፡ ሜዳይ ፣ ቢልልኝ ፡ ማንደፍሮ ፡ ከኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ተማሪዎች ፡ ውስጥ ፡ በትምህርቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ውጤት ፡ ያሳየ ፣ ብርሃኑ ፡ ኪዳኔ ፡ ከእንግሊዘኛ ፡ ዲፕሎማ ፡ ክፍል ፡ በትምህርት ፡ ከፍተኛ ፡ ውጤት ፡ ያሳየ፣ ዓለማየሁ ፡ ጉልላት ፡ ከአማርኛ ፡ ዲፕሎማ ፡ ክፍል ፡ በትምህርቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ውጤት ፡ ያመጣ ፣ ሰይፉ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ ለሕግ ፡ ስነ ፡ ጽሑፍ ፡ (ኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡) የሚሰጠውን ፡ ሽልማት ፡ አግኝቷል ፡ ተባባሪ ፡ የክብሩ ፡ ተካፋይ ፡ ቢልልኝ ፡ ማንደፍሮ ፣ የትምህርቱን ፡ ውጤት ፡ በበለጠ ፡ እያሻሻለ ፡ የሄደ ፡ ተማሪ ፡ ግርማ ፡ ሥላሴ ፡ አርአያ ፣ ተባባሪ ፡ የክብሩ ፡ ተካፋይ ፡ ኤደን ፡ ፋሲልና ፡ ለማ ፡ ጉተማ ፣ ሰይፉ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ ከመደበኛው ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ ውጭ ፡ በሚከናወነው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ ተሳታፊነቱ ፡ ከሌሎች ፡ የላቀ ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ የጄምስ ፡ ሲ ፡ ኤን ፡ ፓልን ፡ ሽልማት ፡ አግኝቷል ።

በኢትዮጵያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎት ፡ መሳተፍ ፡ ከቀረላቸው ፡ ጥቂት ፡ ተማሪዎች ፡ በስተቀር ፡ ሌሎቹ ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ እጩዎች ፡ ከመመረቃቸው ፡ አስቀድሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎት ፡ መካፈላቸው ፡ አሁንም ፡ ይቀጥላል። ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ እንደተደረገው ፡ ሁሉ ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በተለይም ፡ በመንግሥት ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ይመደባሉ ። ሆኖም ፡ ለዲግሪ ፡ እጩዎች ፡ የሆኑ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎት ፡ መካፈል ፡ ያለባቸው ፡ ተማሪዎች ፡ የኛዎቹም ፡ ጭምር ፡ የትምህርት ፡ ገበታቸውን ፡ ለማከናወን ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሲቀራቸው ፡ ለአገልግሎቱ ፡ መላክ ፡ ያለባቸው ፡ መሆኑንና ፡ ይህንኑም ፡ አገልግሎት ፡ ከአዲስ ፡ አበባና ፡ ከአስመራ ፡ ውጭ ፡ መፈጸም ፡ ያለባቸው ፡ መሆኑን ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ ወስኗል ። እስካሁን ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ አገልግሎት ፡ ይሄዱ ፡ የነበሩት ፡ ዲግሪ ፡ ለማግኘት ፡ የሚያበቃቸውን ፡ ትምህርት ፡ ካጠናቀቁ ፡ በኋላ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ አገልግሎቱን ፡ የፈጸሙት ፡ በመናገሻው ፡ ከተማ ፡ ነበር ። የዩኒቨርሲቲው ፡ ውሳኔ (ደንብ) ጥቅም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፡- ተማሪዎች ፡ በገጠር ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሲቆዩ ፡ ስለጠቅላላው ፡ ሁኔታ ፡ ያረጋገጡትንና ፡ የተረዱትን ፡ በትምህርት ፡ ገበታቸው ፡

ላይ ፡ ያቀርቡታል ፡ እንደዚህም ፡ ሲሆን ፡ ራሳቸውና ፡ ሌሎችም ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ የሚማሩት ፡ ተማሪዎች ፡ ወደፊት ፡ የሚኖራቸው ፡ የትምህርት ፡ ልምምድ ፡ ይዳብራል ። በዚህ ፡ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ከሶስተኛ ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎቻችን ፡ ከፊሎቹን ፡ በአገልግሎት ፡ መካፈል ፡ ካለባቸው ፡ የአራተኛ ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎቻችን ፡ ጋር ፡ በመላክ ፡ የዩኒቨርሲቲውን ፡ ውሳኔ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ መከተል ፡ ላይ ፡ ነን ። ወደ ፡ አገልግሎት ፡ የሚላኩት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ሁሉ ፡ የትምህርት ፡ ገበታቸውን፡ ለማከናወን ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የቀራቸው ፡ እስኪሆኑ ፡ ድረስ ፡ በሚቀጥሉት ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ከሶስተኛ ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ለአገልግሎት ፡ የሚላኩት ፡ ቍጥራቸው ፡ እየበረከተ ፡ ይሄዳል ።

ባለፈው ፡ ሰሚስተር ፡ ከየመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የአገልግሎት ፡ ተማሪዎች ፡ እንዲላኩልን ፡ ሲባል ፡ የደረሰን ፡ ጥያቄ ፡ ለአገልግሎት ፡ ከተዘጋጁት ፡ ተማሪዎች ፡ ቍጥር ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ በማለቱ ፡ የተማሪዎቻችንን ፡ ተመራጭነትና ፡ ለመንግሥት ፡ የሚያገለግሉ ፡ የሠለጠኑ ፡ የሕግ ፡ ባለሙያዎች ፡ ያነሱ ፡ መሆናቸውን ፡ ያመለክታል ። ብዙ ፡ ስምምነት ፡ ተደርጐ ፡ አንዳንድ ፡ ሚኒስቴሮችና ፡ ድርጅቶች ፡ የተቆጩ ፡ ቢሆንም ፡ ለሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎት ፡ የመጨረሻው ፡ ድልድል ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፡— ለጭላሎ ፡ የእርሻ ፡ ልማት ፡ ተስፋዬ ፡ ብርሃኔ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መብራት ፡ ኃይል ፡ ባለሥልጣን ፡ ኢሳይያስ ፡ ኃይለማርያም ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ዓለምሰገድ ፡ ተስፋዬ ፡ ገድለ ፡ አማኑኤል ፡ ኪዳነ ፡ ማርያም ፡ ግርማ ፡ ሥላሴ ፡ አርዓያ ፡ ሠይፉ ፡ ተክለማርያምና ፡ ተስፉ ፡ አያና ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አበራ ፡ ደጉ ፡ ዓለሙ ፡ ፎኪዮን ፡ አምሐ ፡ ጽዮን ፡ ዶሜኒኮ ፡ ኤደን ፡ ፋሲል ፡ ኢያሱ ፡ እምነቱ ፡ ፍስሐ ፡ ይመር ፡ ጊዲዮን ፡ አገኘ ፡ ግርማ ፡ ኃይለ ፡ ገብርኤል ፡ ኃይሉ ፡ ቸርነት ፡ ዮሐንስ ፡ ሐብተ ፡ ሥላሴ ፡ ከበደ ፡ ወርቂ ፡ ክፍሌ ፡ ለማ ፡ ወረደ ፡ ወልድ ፡ ወልዴና ፡ ዮሴፍ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ። ለመሬት ይዞታ ፡ ሚኒስቴር ፡ ዓለም ፡ አንተ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴና ቢልልኝ ፡ ማንደፍሮ ፤ ለማዕድን ፡ ሚኒስቴር ፡ ዓለማየሁ ፡ ሠይፉና ፡ ተስፋዬ ፡ ጨምር ።

ከትምህርት ፡ ሰዓት ፡ ውጭ ፡ ተማሪዎች ፡ የሚያከናውኗቸው ፡ ተግባሮች ፡ በብዙ ረገድ ፡ እንዳለፈው ፡ ዓመት ፡ ነበሩ ። በምናደርገው ፡ የመጻሕፍት ፡ ማሳተም ፡ እቅድ ፡ በተለይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔትና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ማጠቃለያ ፡ የተማሪዎች ፡ የትርጉም ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊነት ፡ አላቋረጠም ። የተማሪ ፡ አዘጋጇዎችም ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮችን ፡ በመምረጥና ፡ ሌላም ፡ መጽሔቱን ፡ ለማውጣት ፡ አስፈላጊ ፡ በሆኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡ በመሳተፍ ፡ ጠቃሚ ፡ ዕርዳታ ፡ አድርገዋል ። በማንም ፡ ሳይረዱ ፡ ተማሪዎቹ ፡ ራሳቸው ፡ "ሚዛንና ፡ ሠይፍ" የሚለውን ፡ ዓመታዊ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መጽሐፍ ፡ አሳተሙ ። በብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ማሕበር ፡ እንደወትሮው ፡ ብዙ ፡ ጉዳዮችን ፡ ባያከናውንም ፡ የስብሰባ ፡ ምሽቶችን ፡ አዘጋጅቷል ፡ ተናጋሪዎችን ፡ ጋብዟል ፡ "እናንተው ፡ ፍረዱ" በሚለው ፡ በኢትዮጵያ፡ ቴሌቪዥን ፡ ፕሮግራም ፡ ተሳትፏል ። እንዲሁም ፡ በሕግ ፡ ሕንጻ ፡ በገንዘብ ፡ አሰባሰብ ፡ ረድቷል ።

<u>ስለአስተማሪዎች ፤</u> በዚህ ፡ ዓመት ፡ በኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪና ፡ በእንግሊዘኛ ፡ ዲፕሎማ ፡ ሙሉ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስተምሩ ፡ ሃያ ፡ አስተማሪዎች ፡ በአማርኛ ፡ ዲፕሎማና ፡ በሰርቲፊኬት ፡ የሚያስተምሩ ፡ የከፊል ፡ ጊዜ ፡ አስተማሪዎች ፡ አስራ ፡ ስምንት ፡ነበሩ። እንደ ፡ ትልቅ ፡ መሻሻል ፡ የሚቆጠረው ፡ ሦስት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ለሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ አስተማሪዎች ፡ እንዲሆኑ ፡ መሾማቸው ፡ ነው ። ሦስቱም ፡ በጥሩ ፡ ውጤት ፡ ከሕግ ፡ ፋኩልቲያችን ፡ የተመረቁ ፡ ሲሆኑ ፡ በሚቀጥለው ፡

ዓመት ፡ የዲግሪና ፡ ከዲግሪ ፡ በታች ፡ ያሉትንም ፡ ትምሕርቶች ፡ ያስተምራሉ ። ሙሉ ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ለማስተማር ፡ እነዚህ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ናቸው ፡ በጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ሙሉ ፡ ጊዜ ፡ ከሚያስተምሩት ፡ መምህራን ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሌሎች ይሾማሉ ።

ሙሉ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስተምሩት ፡ አስተማሪዎች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አዳዲስ ፡ የትምህርት ፡ ዘርፎች ፡ ተጨምረዋል ። በዚህ ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ አዳዲስ ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ የትምህርት ፡ ዘርፎች ፡ የሚከተሉት ፡ ነበሩ ፡— ስለግለ ፡ ሰብ ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ፡ (አንደኛ ፡ ዓመት ፡ ሕግ) ፤ የሕዝብ ፡ እንቅስቃሴዎችና ፡ ሕገ — መንግሥታዊ ፡ ለውጥ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ (አንደኛ ፡ ዓመት ፡ ሕግ ፡) ፤ ስለ ፡ ሠራተኛና ፡ አሠሪ ፡ ሕግ ፡ (ሦስተኛና፡ አራተኛ፡ዓመት፡ሕግ፡አማራጭ)፡ማስረጃ፡ (ሦስተኛ፡ዓመት፡) ግብር፡ (አራተኛ፡ዓመት፥ አማራጭ)፤ በአገሮች፡መካከል፡የሚደረግ፡ትራንስአክሽን፡ (አራተኛ፡ዓመት፡አማራጭ)፤ዓለም፡ አቀፍ ፡ የሆኑ ፡ ድርጅቶች ፡ (አራተኛ ፡ ዓመት ፡ አማራጭ) ፤ የከተማ ፡ ችግሮችና ፡ የቀበሌ ፡ አስተዳደር ፡ (አራተኛ ፡ ዓመት ፡ አማራጭ) ። ለሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ እንዲሰጡ ፡ የጸደቁት ፡ የትምህርት ፡ ዘርፎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡— የመንግሥት ፡ ውሎች ፡ (ሦስተኛ ፡ ዓመት ፡ አማራጭ) ፡ የሕግ ፡ ሥራ ፡ በኢትዮጵያ ፡ (አራተኛ ፡ ዓመት) ፤ ለእርሻ ፡ እንዲያመች ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ መሻሻል ፡ (አራተኛ ፡ ዓመት ፡ አማራጭ) ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ ሕግ ፡ (አራተኛ ፡ ዓመት ፡ አማራጭ) ፡ የሕግ ፡ ትንታኔ ፡ (አራተኛ ፡ ዓመት ፡ አማራጭ፡) የእስላም ፡ ሕግ ፡ (አራተኛ ፡ ዓመት ፡ አማራጭ ፡) እንዲሁም ፡ በዚህ፡ በሚመጣው፡ ዓመት ፡ የአስተዳደር ፡ ሕግና ፡ ከፍተኛ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ስለ ፡ ወንጀለኞች፡ የቅጣት ፡ አፈጻጸም) ፡ ለዲፕሎማ ፡ ፕሮግራም ፡ አዲስ ፡ የትምህርት ፡ ዘርፎች ፡ ይሆናሉ ።

ከማስተማር ፡ ሥራቸው ፡ ሌላ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ አስተማሪዎች ፡ ሌሎች ፡ ተግባሮች ፡ አከናውነዋል ። ብዙ ፡ የምርምርና ፡ የጽሑፍ ፡ ሥራ ፡ ሠርተዋል ፤ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚያከናውናቸውን ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ተግባሮች ፡ አላፊ ፡ ሆነው ፡ በመምራት፡ ረድተዋል፡የዩኒቨርሲቲ፡ኰሚቴ፡በሚፈጽማቸው፡አስፈላጊና፡ጊዜን ፡ በሚያጠፉ፡ አድካሚ ፡ ሥራዎች ፡ ተካፋይ ፡ ሆነዋል ፤ እነዚሁ ፡ መምህራን ፡ ከማስተማር ፡ ሥራቸው ፡ ሌላ ፡ ከፈጸሚቸው ፡ ሥራዎች ፡ የሚከተለው ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ አስረጂ ፡ (ምሳሌ) ፡ ሊሆነን ፡ ይችላል ።

ጀምስ ፡ ሲ ፡ ኤን ፡ ፖል ፤ የዩኒቨርሲቲው ፡ አካዴሚክ ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚደንት፡ ሲሆኑ ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አባል ፡ ናቸው ፡ እሳቸውም ፡ ለሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ምክር ፡ ከመለገሳቸውም ፡ በላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መስፋፋት ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ያዘጋጁትን ፡ መጽሐፋቸውን ፡ አሳትመው ፡ ሁለተኛውን ፡ ቮልዩም ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ለመፈጸም ፡ ችለዋል ።

ሪቻርድ ፡ ካሚንግስ ፤ ከዓመቱ ፡ መጀመሪያ ፡ አጋማሽ ፡ ወዲህ ፡ በፋኩልቲው ፡ በኩል ፡ የመጽሔቱ ፡ ዋና ፡ አዘጋጅ ፡ ሆነው ፡ መሥራት ፡ ጀምረዋል ። ለኢትዮጵያ ሕገ ፡ መንግሥት ዕድገት ፡ ማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ተጨማሪ ፡ ጽሑፎችን ፡ እንዲሁም ፡ በመጽሔቱ ፡ የሚታተሙ ፡ አያሌ ፡ አንቀጾችን ፡ አዘጋጅተዋል ።

ሃሪሰን ፡ ዳኒንግ ፤ ረዳት ፡ ዲን ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ ትምህርት ፡ ነክ ፡ ላል ሆነው ፡ የአስተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ በሙሉ ፡ ሃላፊ ፡ ናቸው ። በተጨማሪ ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ (ካሪኩለም ፡) ጉባኤ ፡ ሊቀ ፡ መንበርና ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ የሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ አባል ፡ ናቸው ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቅሙ

ትን ፡ ሀብቶች ፡ ለማስለቀቅ ፡ የሚጠቀሙባቸውን ፡ ሕጎች ፡ እያነፃፀረ ፡ የሚመረምር ፡ አንቀጽ ፡ አዘጋጅተዋል ።

እንዲሁም ፡ የጥንት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርዶችን ፡ ለመሰብሰብ ፡ ፋኩልቲው ፡ የጀመረውን ፡ ሥራ ፡ በተቆጣጣሪነት ፡ ሰርተዋል ።

ዊልያም ፡ ዩዊንግ ፤ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተማሪዎችና ፡ ፋኩልቲ ፡ ግንኙነት ፡ ኮሚቴ ፡ ሊቀ ፡ መንበርና ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ተማሪዎች ፡ ጉዳይ ፡ አጥኚ ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፡ ሲሆኑ ፡ እንዲሁም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ማጠቃለያ ፡ ፕሮግራም ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ናቸው ።

ስታንሊ ፡ ፊሸር ፤ የምርመራና ፡ የስነ ፡ ጽሑፍ ፡ አዘጋጅ ፡ ኮሚቴ ፡ ሊቀ ፡ መንበርና ፡ የሕግ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ፕሮግራም ፡ ተቆጣጣሪ ፡ ናቸው ። በዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ሰፋ ፡ ያለውን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ስነ ፡ ስርዓት ፡ ማብራሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎችና ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ የደረሱትን መጽሐፍ ፡ ወደ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ለመላክ ፡ በቅተዋል ።

ዣን ፡ ዴንስ ፡ ጋኞን ፤ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስለአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ሕግና ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ ኃላፊነት ፡ ማስተማሪያ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ተጀምረው ፡ የነበሩትን ፡ ጽሑፎች ፡ ከፍጻሜ ፡ አድርሰዋል ። እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ሕግ ፡ አያሌ ፡ አንቀጾችን ፡ በመጻፍ ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

ፍራንክ ፡ ሆሮዊትስ ፤ በኢትዮጵያ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ካስተማሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፋኩልቲአችን ፡ የመጡ ፡ የሰላም ፡ ጓድ ፡ አባል ፡ ናቸው ። ተማሪዎቹ ፡ በጽሑፍ ፡ የሚያቀርቡትን ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ በማረምና ፡ ተማሪዎቹን ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ በማነጋገር ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ አገልግሎትን ፡ ሲሰጡ ፡ ደካማ ፡ ውጤት ፡ ያላቸውን ፡ ተማሪዎች ፡ የተለየ ፡ ትምህርት ፡ በመስጠት ፡ ረድተዋል ። ሚስተር ፡ ማርሻልንም ፡ ተማሪዎችን ፡ በመምከር ፡ ረገድ ፡ ለሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ የመኖሪያ ፡ ቤት ፡ ማሰሪያ ፡ መዋጮ ፡ በመሰብሰብም ፡ ረድተዋል ።

ሚክቼልድ ፡ ኢመንኮተር ፤ የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ባደረገው ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታ ፡ በመጠቀም ፡ አንድ ፡ ሰሜስተር ፡ በሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቆይተው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ ጀምረውት ፡ የነበረውን ፡ መጽሐፍ ፡ ፈጽመዋል ።

ማይክል ፡ ኪንድረድ ፤ እስከ ፡ አንደኛው ፡ ሰሜስተር ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ምክትል ፡ ዲን ፡ ነበሩ ፡ አሁንም ፡ የመምህራን ፡ ጉባኤ ፡ ሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ኮሚቴ ፡ ጸሐፊ ፡ ናቸው ፡ ለወደፊቱ ፡ የሚታተሙ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ሕግ ፡ የሚመለከቱ ፡ ሁለት ጠቃሚ ፡ አንቀጾችን ፡ ተርጉመዋል ። ለአቅመ ፡ አዳም ፡ ስላላደረሱ ፡ ሰዎች ፡ መብት ፡ አንድ ፡ አንቀጽ ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

ሎረንስ ፡ ኖውልስ ፤ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ኮሚቴ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ናቸው ። እሳቸውም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ስነ ፡ ስርዓት ፡ ሕግ ፡ ማስተማሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ጽሑፎችን ፡ አዘጋጅተው ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ሥራ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ አንቀጽ ፡ ጽፈዋል ።

ጆርጅ ፡ ክሽቹኖቪች ፤ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሁለት ፡ አንቀጽ ፡ ጽፈው ፡ በሁለተኛው ፡ ሰሜስተር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ስር ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚፈጠሩ ፡ ግዴታዎች ፡ ያላቸውን ፡ አቋም ፡ የሚመረምረውን ፡ መጽሐፋቸውን ፡ ለመጻፍ ፡ በእረፍት ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

ጆን ፡ ማርሻል ፤ ከሁለተኛው ፡ ሰሚስተር ፡ ጀምረው ፡ ምክትል ፡ ዲን ፡ ሆነው ፡ መስራት ፡ ስለ ፡ ጀመሩ ፡ ተማሪዎችን ፡ መምከር ፡ መመዝገብ ፡ አዲስ ፡ የሚገቡትን ፡ ተማሪዎች ፡ መምረጥ ፡ የሳቸው ፡ አላፊነት ፡ ነው ። በተጨማሪ ፡ የኤክስቴሽን ፡ ፕሮግራም ፡ አላፊና ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ የሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ አባል ፡ ናቸው ፤ ስለ ፡ አስተዳደር ፡ ሕግና ፡ ስለ ፡ ግብር ፡ ለሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፎችንና ፡ ኢያሌ ፡ አንቀጾችን ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

ፖል ፡ ማካርቲ ፤ ፋኩልቲው ፡ ለሚያሳትማቸው ፡ ጽሑፎች ፡ የአስተዳደር ፡ አላፊ ፡ ናቸው ። በሕግ ፡ ያልታወቁ ፡ (ዲ ፡ ፋክቶ) የንግድ ፡ ማህበሮች ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ አንድ ፡ አንቀጽ ፡ ጽፈዋል ።

ፖል ፡ ፓኛር ፤ በአፍሪቃ ፡ የሕግ ፡ ዕድገት ፡ ማዕከላዊ ፡ ድርጅት ፡ የዶክተር ፡ ቫንደር ፡ ሊንደን ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ ሰርተዋል ።

ፒተር ፡ ሳንድ፤ የቤተ፡ መጻሕፍት ፡ ኮሚቴ፡ ሊቀ ፡ መንበር፡ ናቸው። ስለ ፡ ኢትዮጵያ፡ ሕግ ፡ በዛ ፡ ያሉ ፡ አንቀጾችን ፡ ጽፈዋል ። እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ውርስና ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሕግ ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፎችን ፡ በተለይም ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ አነስተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

ኖርመን ፡ ሲንገር ፤ ተማሪዎችን ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ የተማሪዎቹ ፡ አማካሪ ፡ ነበሩ ። ሕግና ፡ አንትሮፖሎጂ ፡ ጠቀስ ፡ በሆኑ ፡ ጉዳዮች ፡ ምርምርና ፡ ጥናት ፡ አድርገዋል ። ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አቋም ፡ ሦስት ፡ ከፍጻሜ ፡ የደረሱ ፡ ወይም ፡ የተቃረቡ ፡ ሰፊ ፡ ጽሑፎች ፡ አዘጋጅተዋል ።

ዘካርያስ ፡ ሱንድስትሮም ፤ በአገሮች ፡ መካከል ፡ ስለሚደረግ ፡ ትራንዝአክሽን ፡ ሦስት ፡ ቮልዩም ፡ የያዘ ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ አዘጋጅተዋል ።

ፒተር ፡ ስትራውስ ፤ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ በሚመለከተው ፡ ሥራ ፡ በኩል ፡ ዋናውን ፡ ኃላፊነት ፡ በመውሰድ ፡ ሰርተዋል ። በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የሚታተመውን ፡ አዲሱን ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የእንግሊዘኛ ፡ ትርጉም ፡ አርመዋል ። ለወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የተዘጋጀውን ፡ የማስተማሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ አክለውበታል ። በተጨማሪ ፡ የአዲስ ፡ ተቀጣሪዎች ፡ የዕድገት ፡ ኰሚቴና ፡ የኦነር ፡ ቦርድ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ናቸው ።

ማይክል ፡ ቶፒንግ ፤ የሮማውያን ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ፡ የሚል ፡ አነስተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ አዘጋጅተዋል ። ከፒተር ፡ ስትራውስ ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ እንዴት ፡ እየደሚሰጥና ፡ እንዲሁም ፡ የኢትዮጵያን ፡ የኢንሹራንስ ፡ ሕግ ፡ የሚመረምሩ ፡ አንቀጾች ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

ዣክ ፡ ቫንደርሊንደን ፤ በአፍሪቃ ፡ የሕግ ፡ ዕድገት ፡ መስፋፋት ፡ ጥናት ፡ ማዕከላዊ ፡ ድርጅት ፡ ድሬክተር ፡ ናቸው ። ስለ ፡ ሰዎችና ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ሕግ ፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ አነስተኛ ፡ መጽሐፎችን ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ናቸው ።

የኤክስቴንሽን ፡ ፕሮግራም ፡ ከተጀመረ ፡ ወዲህ ፡ ሌላ ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ ቢኖርባቸውም ፡ ለማስተማር ፡ ከልብ ፡ የሚጥሩ ፡ የዲፕሎማንና ፡ የሰርቲፊኬትን ፡ ፕሮግራም የሚያስተምሩ ፡ የገሚስ ፡ ጊዜ ፡ መምህራን ፡ በማግኘታችን ፡ በጣም ፡ ዕድለኞች ፡ ነን ። ሐረር ፡ የሚገኙት ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ዳምጤ ፡ አሥመራ ፡ የሚያስተምሩት ፡ አቶ ፡ ብርሃኑ ፡ ባይህና ፡ አቶ ፡ ካሣ ፡ በየነ ፡ እንዲሁም ፡ ጂማ ፡ ያስተምሩ ፡ የነበሩትና ፡ በቅርቡ ፡ ለልዩ ፡ ትምህርት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሄዱት ፡ አቶ ፡ አባቢያ ፡ አባ

ጆቢር ፡ የተለየ ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ። እነዚህ ፡ መምህራን ፡ አዳዲስ ፡ ፕሮግራሞች ፡ ከመክፈታቸውም ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ የአስተዳደር ፡ ሥራም ፡ ነበረባቸው ።

እንዲሁም ፡ አዳጋችና ፡ አድካሚ ፡ የሆነውን ፡ የምክትል ፡ አስተዳዳሪነትንና ፡ የሬጅስትራሩን ፡ ሥራ ፡ በሚገባ ፡ ያከናወኑትን ፡ ሚሲዝ ፡ ጆርጅ ፡ ክሽቼኖቪችንና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሕግ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ ማጠቃለያ ፡ በማዘጋጀት ፡ በጣም ፡ የረዱንን ፡ ሚሲዝ ፡ ጆሴፍ ፡ ግሪንፊልድን ፡ ሳናመሰግናቸው ፡ አናልፍም ። ከሙሉ ፡ ጊዜ ፡ መምህራኖች ፡ ውስጥ ፡ ስምንቱ ፡ የሥራ ፡ ጊዜአቸውን ፡ ፈጽመው ፡ ወደየሃገራቸው ፡ ተመልሰዋል ። ከነሱም ፡ መካከል ፡ አራቱ ፡ ሕግ ፡ የማስተማራቸውን ፡ ሥራ ፡ ይቀጥላሉ ። ፒተር ፡ ሳንድ ፡ በማክጊል ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ስታንሊ ፡ ፊሸርና ፡ ፖል ፡ ማካርቲ ፡ በቦስተን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ሎረንስ ፡ ኖውልስ ፡ ደግሞ ፡ በሉዊቪል ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ያስተምራሉ ። ፒተር ፡ ስትራውስ ፡ በአሜሪካ ፡ መንግሥት ጠቅላይ ፡ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይሠራሉ ። ዣን ፡ ዴንስ ፡ ጋኞን ፡ በሞንትሪኦል ፡ የራሳቸውን ፡ የሕግ ፡ አማካሪነት ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ። ኖርማን ፡ ሲንገር በሃርቫርድ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርታቸውን ፡ ሲቀጥሉ ፡ ፍራንክ ፡ ሆርዊትስ፡ ደግሞ ፡ ያቋረጡትን ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በካሊፎርኒያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ይቀጥላሉ ። በተጨማሪ ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍታችን ፡ ሐላፊ ፡ የነበሩት ፡ አለን ፡ ባትለር ፡ በሆንግ ፡ ኮንግ ፡ የሚገኘው ፡ የቹንግ ፡ ቺ ፡ ኰሌጅ ፡ ዋና ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ኃላፊ ፡ ሆነው ፡ ለመሥራት ፡ ወደዚያው ፡ ሄደዋል ።

## ከውጭ ፡ አገር ፡ የሚሰጠን ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታ ።

አንድ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያለው ፡ አዲስ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መመሥረት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ይጠይቃል ። የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ይህንን ፡ አሁን ፡ ያለውን ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ለመመስረት ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታትና ፡ ድርጅቶች ፡ ሰፊ ፡ ዕርዳታ ፡ አግኝቷል ። ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ አብዛኛውን ፡ ዕርዳታ ፡ የሰጠው ፡ የፎርድ ፡ ድርጅት ፡ ሲሆን ፡ ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የሰጠውን ፡ ዕርዳታ ፡ በማከል ፡ ለ፲፱፻፷፰-፷፱ ፡ እና ፡ ፲፱፻፷፱-፸ ፡ የትምህርት ፡ ዓመታት ፡ የሚሆን ፡ አዲስ ፡ የገንዘብ ፡ ዕርዳታ ፡ ለግሶልናል ። ከውጭ ፡ ለምናገኘው ፡ ዕርዳታ ፡ ምስጋናችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

## ቤተ ፡ መጻሕፍትና ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ መዛግብት ።

ቤተ ፡ መጻሕፍታችን ፡ በየቀኑ ፡ እያደገ ፡ ይሄዳል ። እንዲላኩልን ፡ ካዘዝናቸው መጻሕፍት ፡ ጋር ፡ በቤተ ፡ መጻሕፍታችን ፡ ውስጥ ፡ ፲፭ሺ ፡ መጻሕፍት ፡ ይገኙበታል ። በተጨማሪ ፡ ፫፻ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጽሔቶችን ፡ እንቀበላለን ። በሚመጡት ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ለሚደርሱን ፡ መጻሕፍት ፡ ስፍራ ፡ እንድናዘጋጅ ፡ በማለት ፡ በሕንፃው ፡ በስተ ፡ ምዕራብ ፡ የሚገኘውን ፡ ቨረንዳ ፡ በግንብ ፡ አጥረነዋል ። ቤተ ፡ መጻሕፍቱን ፡ ከሚያደረጁት ፡ ተጨማሪዎች ፡ አንዱ ፡ በዶክተር ፡ ዣክ ፡ ቫንደርሊንደን ፡ ተቆጣጣሪነት ስር ፡ የሚገኘው ፡ የቤልጊክ ፡ መንግሥት ፡ ያቋቋመው ፡ የአፍሪቃን ፡ የሕግ ፡ መስፋፋት ፡ የሚያጠናው ፡ ድርጅት በማይክሮ ፡ ፊልም ፡ አንስቶ ፡ የሰበሰባቸው ከልዩ ፡ ልዩ ፡ የአፍሪቃ ፡ አገሮች ፡ የተውጣጡ ፡ የሕግ ፡ ጽሑፎች ፡ ይሆናሉ ። በዓመቱ ፡ መጀመሪያ ፡ አቅራቢያ ፡ ከነዚህ ፡ ፊልሞች ፡ ጥቂቶቹን ፡ ፋኩልቲው ፡ ተረክቧል ፡ ወደፊትም ፡ በየጊዜው ፡ ይረከባል ። እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ድርጅቱ ፡ የሚሰበስበው ፡ ከ፲፱፻፵፯ ፡ ወዲህ ፡ የወጡትን ፡ ሕጎችና ፡ የተጻፉትን ፡ አንቀጾች ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ስላገኘ ፡ ከ፲፱፻ ፡ ጀምሮ ፡ ያሉትን ፡ ለመሰ

ሰብ ፡ አቅዷል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ድርጅቱ ፡ ስለ ፡ አፍሪቃ ፡ ሕግ ፡ የተጻፉትን ፡ አንቀጾችና ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ ጽሑፎችን ፡ ሰፊ ፡ ዝርዝር ፡ በማሰናዳት ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡ የመጀመሪያው ፡ ዝርዝር ፡ ከጥቂት ፡ ወራት ፡ በፊት ፡ ታትሞ ፡ ወጥቷል ።

## የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ።

በመጀመሪያው ፡ ሰሚስተር ፡ የተማሪዎቻችን ፡ መኖሪያና ፡ መገናኛ ፡ የሚሆነው ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ሰዎችና ፡ ድርጅቶች ፡ በለገሱት ፡ ገንዘብ ፡ መሰራት ፡ ጀመረ ። መጀመሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሊሠራበት ፡ ከታቀደው ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ የቆሻሻ ፡ ማስተላለፊያ ፡ ቧንቧ ፡ እንዲሰራ ፡ ስለተወሰነ ፡ ሥራውን ፡ ትንሽ ፡ ሊያዘገየውና ፡ የሕንፃውንም ፡ ዋጋ ፡ በመጠኑ ፡ ከፍ ፡ ሊያደርገው ፡ ችሏል ። የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ በዩኒቨርሲቲው ፡ ቅጽር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ከመማሪያው ፡ ክፍሎች ፡ አያሌ ፡ መቶ ፡ ሜትሮች ፡ ርቆ ፡ ይገኛል ። ሥራው ፡ በሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ ትምህርት፡ በሚጀመርበት ፡ ሰሞን ፡ እንደሚፈጸም ፡ ይጠበቃል ። የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ይህ ፡ በጣም፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ቤት ፡ እንዲሠራ ፡ የረዱትን ፡ ወዳጆቹን ፡ ሁሉ ፡ ከልብ ፡ ያመሰግናል ። ዩኒቨርሲቲው ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ሕንፃዎች ፡ መካከል ፡ በሕዝብ ፡ መዋጮ ፡ የተሠራው ፡ ይህ ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ነው ። የፋኩልቲው ፡ ፍላጐት ፡ ሕንፃው ፡ የተማሪዎቹ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ብቻ፡ ሳይሆን ፡በሕግ፡ ሥራ ፡ የሚካፈሉ ፡ ሁሉ ፡ ጠበቆች ፡ ዳኞችም ሆኑ ፡ ተማሪዎች ፡ የሚሰበሰቡበትና ፡ ሃሳብ ፡ ለሃሳብ ፡ የሚለዋወጡበት ስፍራ እንዲሆን ፡ ነው ።

## ፋኩልቲው ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ነገሮችና ፡ ያለበት ፡ ችግር ።

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በአፍሪቃ ፡ ውስጥ ፡ በትምህርት ፡ ረገድ ፡ አስደናቂ ፡ ሆነው ፡ ከተገኙት ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በአምስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በአፍሪቃ ፡ አህጉር ፡ ካሉት ፡ ከማናቸውም ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ጋር ፡ የሚወዳደር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መመስረቱ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ባለንበት ፡ ደረጃ ፡ ለመቀጠል ፡ ወይም ፡ ለማሻሻል ፡ ከተፈለገ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ነገሮችና ፡ ያለበትን ፡ ችግር ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ተገንዝበን ፡ መፍትሔ ፡ መፈለግ ፡ ያሻናል ። ባለፈው ፡ ብቻ ፡ ተደስቶ ፡ የወደፊቱን ፡ ችላ ፡ ማለት ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንደሚጐትተውና ፡ ቀስ ፡ በቀስም ፡ ደረጃውን ፡ ዝቅ ፡ እንደሚያደርገው፡ አይካድም ። ያጋጠሙንን ፡ ችግሮች ፡ ተገንዝበን ፡ ለቀድሞ ፡ ተማሪዎቻችንና ፡ ከዩኒቨርሲቲው ፡ ውጭ ፡ ለሚገኙት ፡ ወዳጆቻችን ፡ መግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የትምህርት ፡ መስፋፋት ፡ በተለይም ፡ ሕግን ፡ የመሰለ ፡ ትምህርት ፡ ለማስፋፋት ፡ ከብዙ ፡ አቅጣጫ ፡ መግባባትንና ፡ መረዳዳትን ፡ ስለሚጠይቅ ፡ ነው ።

በኔ ፡ አስተያየት ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ከሚያስፈልጉት ፡ ነገሮችና ፡ ካጋጠሙት፡ ችግሮች ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፤

፩/ አብዛኛዎቹ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ፡ መምህራን፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እንዲሆኑ ፡ ማድረግ። አሁን ፡ ያለብን ፡ ትልቁ ፡ ችግር ፡ ከፍተኛ ፡ ችሎታ ፡ያላቸውን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መምህራን ፡ ማበርከት ፡ ነው ። ሊስፋፉ ፡ የሚችል ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ፋኩልቲአችን ፡ ለመሳብ ፡ እንደሚችል ፡ እተማመናለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልባቸውን ፡ ጀማሪዎች ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያላቸው ፡ መምህራንና ፡ ሊቃውንት ፡ እንዲሆኑ ፡ ማድረግ ፡ ይበልጥ ፡ አዳጋች ፡ ነው ። አዲሶቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መምህራኖቻችን ፡ ዕርዳ

ታና ፡ ማበረታቻ ፡ ተገቢው፡ አበልና ፡ ማዕረግ፡ሲያስፈልግም፡ውጭ፡አገር፡ ሄደው ፡ ትምህርታቸውን ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ዕድል ፡ እንዲኖራቸው ፡ ማድረግ ፡ ብቁ ፡ ሆነው ፡ ሲገኙም ፡ ዕድገት ፡ መስጠት ፡ ይገባቸዋል ። እንዲሁም ፡ የሚያስተምሩበት ፡ ጊዜ ፡ ብዛት ፡ ምርምር ፡ ለማድረግና ፡ ለመጻፍ ፡ የሚያስችላቸው ፡ ሆኖ ፡ የጻፉት ፡ ጥሩ ፡ ከሆነ ፡ መታተም ፡ ይገባዋል ። ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ግን ፡ ዕድልና ፡ ዕርዳታ ፡ ይሰጣቸው ፡ እንጂ ፡ ውጤቱ ፡ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ በሚያሳዩት ፡ የሥራ ፡ ትጋትና ፡ ፍላጐት ፡ መጠን ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑ ፡ አይቀርም ።

፪/ የዲግሪ ፡ ተማሪዎች ፡ ብዛት ፡ ከፍ ፡ ማለት ፡ አለበት ። ኢትዮጵያ ፡ ከሌሎች ፡ የአፍሪካ ፡ አገሮች ፡ ይልቅ ፡ በደንብ ፡ የተማሩ ፡ ጠበቆችና ፡ ዳኞች ፡ ያስፈልጓታል ። አሁን ፡ ካሏት ፡ 1,600 ፡ ዳኞች ፡ ውስጥ ፡ ከዩኒቨርሲቲ ፡ ተመርቀው ፡ የወጡ ፡ 6 ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፤ የሥራ ፡ ፈቃድ ፡ ካላቸው ፡ 2,000 ፡ ጠበቆች ፡ ውስጥም ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ ቁጥራቸው ፡ ከዚህ ፡ ያነሰ ፡ ነው ። በየሚኒስቴሮቹና ፡ በመንግሥት ፡ ድርጅቶችም ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ።

ከዲግሪ ፡ በታች ፡ የከፈትናቸው ፡ ፕሮግራሞች ፡ ለጊዜው ፡ ይኸንን ፡ ችግር ፡ በመጠኑ ፡ ይቋቋሙታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ። ስለዚህም ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ ዲግሪ ፡ ተማሪዎች ፡ ቁጥር ፡ ከፍ ፡ ማለት ፡ አለበት ። ሆኖም ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ በቂ ፡ የዲግሪ ፡ ተማሪዎች ፡ ስለሌሉት ፡ ይኸንን ፡ ዓላማ ፡ ከግብ ፡ ለማድረስ ፡ አልቻለም ። አሁን ፡ ባለን ፡ ድርጅት ፡ ካሉን ፡ ተማሪዎች ፡ እጥፍ ያለአንዳች ፡ ችግር ፡ ለማስተማር ፡ ብንችልም ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ ፋኩልቲአችን ፡ ለመግባት ፡ የሚፈልጉትን ፡ ተማሪዎች ፡ በሙሉ ፡ ስለማይልክልንና ፡ በቂ ፡ ሰው ፡ ስለማይመድብልን ፡ ይኸን ፡ ለማድረግ ፡ አልቻልንም ። ይህ ፡ ችግር ፡ ሊወገድ ፡ የሚችለው ፡ ሕግ ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ለአገሪቱ ፡ የሚሰጡት ፡ አገልግሎትና ፡ አስፈላጊነታቸው ፡ በጥንቃቄ ፡ ተጠንቶ ፡ ካሁን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የተማሪዎች ፡ ቁጥር ፡ ለሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ሲመደብና ፡ የኛም ፡ ፋኩልቲ ፡ ሆነ ፡ ሌሎች ፡ ፋኩልቲዎች ፡ እንደየፍላጐታቸው ፡ ሰው ፡ መምረጥ ፡ ይችሉ ፡ ዘንድ ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ ተማሪዎች ፡ ጠቅላላ ፡ ብዛት ፡ ከፍ ፡ ሲል፡ ነው ።

፫/ ከኢትዮጵያ ፡ ጊዜያዊ ፡ ችግሮች ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ መመርመርና ፡ ስለነዚሁ፡ ችግሮች ፡ መጻፍ ፡ ያስፈልጋል ። ፋኩልቲአችን ፡ ለማስተማሪያ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ጽሑፎች ፡ በሚገባ ፡ አሰናድቷል ። ከእንግዲህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያለባትን ፡ ሕጋዊ ፡ ችግሮች ፡ በተለይም ፡ ሕግ ፡ ከዕድገት ፡ መፋጠን ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ወደሚያጠና ፡ ምርምር ፡ ማዘንበል ፡ አለብን ፡ ባይ ፡ ነኝ ። ይህ ፡ አዳጋች ፡ ሥራ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በኅብረተ ፡ ሰብና ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ችሎታ ፡ የሚያስፈልገውና ፡ በነዚህም ፡ ትምህርቶች ፡ ሞያተኞች ፡ መካከል ፡ መተባበርን ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በመልማት ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ አገሮች ፡ ሕግ ፡ ማወቅንና ፡ ሕግን ፡ ለልማታቸው ፡ እንዴት ፡ እንደተጠቀሙበት ፡ ማወቅን ፡ ይጠይቃል ። ሥራው ፡ አዳጋች ፡ ነው ፡ በደንብ ፡ ከተሠራ ፡ ግን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሚሰጠው ፡ ጥቅም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

## <u>የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ መሻሻል ፡</u>

፩/ ሰፊና ፡ አጥጋቢ ፡ የኤል ፡ ኤል ፡ ቢ ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ አለን ። ሆኖም ፡ ፕሮግራሙ ፡ አብዛኛውን ፡ የግለ ፡ ሰብን ፡ ሕግ ፡ ወደሚመለከቱት ፡ ትምህርቶች ፡ ስለሚያዘነብል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያሉባትን ፡ ችግሮች ፡ ለመመርመርና ፡ ለማጥናት ፡ በቂ ፡

ጊዜ ፡ አይሰጥም ። አንዱ ፡ ትልቅ ፡ እንቅፋት ፡ (ችግር) ፡ አሁን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉት፡ ሐሳቦችና ፡ እነሱን ፡ ለማሻሻል ፡ የሚቀርቡት ፡ ሃሳቦች ፡ ያስከተሉትንና ፡ የሚያስከትሉትን ፡ ውጤት ፡ ለማወቅ ፡ የሚያስችል ፡ መረጃ ፡ አለማግኘቱ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ሕብረተ ፡ ሰብ ፡ አቋም ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ መሆኑን ፡ አውቆ ፡ በዚያ ፡ መሠረት ፡ ሕጉ ፡ እንደዚህ ፡ ወይም ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ መስመር ፡ መከተል ፡ ያስፈልጋል ፡ ብሎ ፡ ለመናገር ፡ የሚያስችል ፡ ትክክለኛና ፡ የተብራራ ፡ ጽሑፍ ፡ እጅግም ፡ አይገኝም ። ስለ ዚህ ፡ የትምህርቱ ፡ ፕሮግራም ፡ መሻሻል ፡ በከፊል ፡ በሶስተኛው ፡ ቁጥር ፡ ከተገለጸው ፡ በሕግ ፡ ሊቃውንትና ፡ በሕብረተ ፡ ሰብ ፡ ትምህርት ፡ ሊቃውንት ፡ ምርምርና ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ። በሰርቲፊኬትና ፡ በዲፕሎማ ፡ ደረጃ ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ፡ ልዩ ፡ ችግር ፡ ይፈጥራል ፡ ምክንያቱም ፡ እነዚህን ፡ ፕሮግራሞች ፡ ስናስተምር ፡ ዓላማችን ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ይኸንንስ ፡ ዓላማ ፡ ከግብ ፡ ለማድረስ ፡ የትኛውን ፡ የትምህርት ፡ ዓይነት ፡ መስጠት ፡ ይገባናል ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ ጠለቅ ፡ አድርገን ፡ መመርመር ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ነው ። በተለይም ፡ በሰርቲፊኬትና ፡ በዲፕሎማ፡ ፕሮግራሞች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነትና ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ተማሪዎች ፡ ፕሮግራሞቹን ፡ መከታተል ፡ እንደሚችሉ ፡ እንደገና ፡ መመርመር ፡ ያስፈልጋል ። እነዚህን ፡ ፕሮግራሞች ፡ ለመከታተል ፡ የሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፡ ድርጅቱም ፡ ልዩና ፡ አስደናቂ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ፕሮግራሞች ፡ ሊያበረክቱት ፡ የሚችሉትን ፡ ውጤት ፡ እንደሚሰጡን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለብን ።

፰/ የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ ማሕበር ፡ የሚንቀሳቀስና ፡ ፍሬያማ ፡ መሆን ፡ አለበት። መቋቋሙን ፡ ማኅበሩ ፡ ተቋቁሟል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ምክንያቱም ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ የሰፈረ ፡ ድርጅት ፡ ዋጋ ፡ የለውም ። ማኅበሩ ፡ ዳኞችና ፡ ጠበቆች ፡ በሥራቸው ፡ ላይ ፡ ሊከተሏቸው ፡ የሚገባቸውን ፡ ደንቦች ፡ እንደሚያወጣ ፤ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚገጥሟቸውን ፡ ችግሮች ፡ እንደሚያጠናና ፡ ሕግ ፡ በተማሩ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የአንድነትን ፡ መንፈስ ፡ እንደሚፈጥር ፡ ይጠበቃል ። በየጊዜው ፡ ደጋግሞ ፡ መሰብሰብ ፡ ያስፈልገዋል ።

ማኅበሩ ፡ ከፋኩልቲው ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ለጠበቆች ፡ የሚታደሉ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የተደረሱ ፡ አጫጭር ፡ ጽሑፎችንና ፡ መጻሕፍቶችን ፡ ሊያዘጋጅና ፡ ሊያድል ፡ ይችላል ። አንድ ፡ ላይ ፡ በመሰብሰብም ፡ ሆነ ፡ ለየብቻ ፡ በመወያየት ፡ ተማሪዎቻችን ፡ ከትምህርት ፡ ዓለም ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ዓለም ፡ ለመግባት ፡ የሚጠቅማቸውን ፡ ምክር ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

፱/ ድርጅቱ ፡ የተሟላ ፡ ሕንጻ ፡ ያስፈልገናል ።

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያሉን ፡ የምንሠራባቸው ፡ ሕንፃዎች ፡ ያረጁ ፡ በደንብ ፡ ያልተጠበቁና ፡ ለአንድ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የማይስማሙ ፡ ናቸው ። ለጊዜው ፡ ባለን ፡ ለመቀጠል ፡ እንችላለን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የመማሪያ ፡ ክፍሎችንና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱን ፡ እንዲሁም ፡ ለጥናት ፡ ምቹ ፡ የሆነና ፡ ቁጥራቸው ፡ ከፍ ፡ ለሚለው ፡ ተማሪዎቻችን ፡ የሚበቃ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አጠቃሎ ፡ የሚይዝ ፡ አዲስ ፡ ሕንጻ ፡ በቅርቡ ፡ መሠራት ፡ አለበት ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ስፍራ ፡ ጠቦናል ፡ የተማሪዎች ፡ ቁጥር ፡ እየጨመረ ፡ በሚሄድበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ካሁኑ ፡ የባሰ ፡ ይሆናል ። ማንኛውም ፡ ለሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የታቀደ ፡ ሕንጻ ፡ በፋኩልቲው ፡ ቁጥጥር ፡ ስር ፡ የሚገኝ ፡ የተሟላ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መያዝ ፡ አለበት ።

፲/ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ከውጭ ፡ ዓለም ፡ ጋር ፡ ጠቃሚ ፡ ግንኙነትን ፡ መቀጠል ፡ አለበት ። በሚመጡት ፡ አስር ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ የራሱን፡

ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ በመከታተል ፡ በውጭ ፡ ከሚደረገው ፡ የትምህርት ፡ ዕድገት ፡ ጋር ፡ ግንኙነቱን ፡ አቋርጦ ፡ እንዳይቀር ፡ የሚያሰጋ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ይህ ፡ ትልቅ ፡ አገር ፡ ነው ፤ ትልልቅ ፡ አገሮችም ፡ ትምህርት ፡ ቤታቸውን ፡ በራሳቸው ፡ መምህራን ፡ በሚያካሒዱበት ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዝንባሌ ፡ ያድርባቸዋል ። እውነት ፡ ነው ፡ ፋኩልቲው ፡ ዓይነተኛው ፡ ተግባሩ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ ችግሮች ፡ መመርመርና ፡ ማስወገድ ፡ ነው ፤ ሆኖም ፡ ይህንን ፡ መስመር ፡ ብቻ ፡ የተከተለ ፡ እንደሆነ ፡ የሚሰጠው ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ይሄዳል ። የሚሻለው ፡ ኢትዮጵያውያኑ ፡ መምህራን ፡ አግባብ ፡ ያላቸውን ፡ የውጭ ፡ አገሮችን ፡ በተለይም ፡ የአፍሪቃ ፡ አገሮችን ፡ ሕጎች ፡ ቢያውቁ ፣ ስለ ፡ ሕግ ፡ የሚደረሱትንም ፡ ጽሑፎች ፡ ቢከታተሉና ፡ ከየአገሮቹ ፡ የሕግ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ቢተዋወቁ ፡ ነው ። ይህ ፡ ቢደረግ ፡ የመምህራኑ ፡ ዕውቀት ፡ ይጎለምሳል ። የኢትዮጵያንም ፡ ሕግ ፡ ለመመርመር ፡ ሰፊና ፡ ጠቃሚ ፡ ምንጭ ፡ ይኖራቸዋል ። በተጨማሪ ፡ ንቁ ፡ አእምሮ ፡ ያላቸውና ፡ ኢትዮጵያውያንንም ፡ በኢንተርናሽናል ፡ የትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ለመወከልና ፡ ለማስጠራት ፡ ብቁ ፡ ያደርጋቸዋል ።